# በሀዲስ አለማዬሁ ልዩ አዳሪ ት/ቤት ለ9ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ወርክሽት

(ማስታወሻ ፡- ጥያቄው ከሁሉም የትምህርት ይዘት የተዘጋጀ በመሆኑ ሙሉ የመፅሀፉን ይዘቶች በማንበብ ጥቄዎችን ስራ/ሪ)

I. **ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ብቻ ምረጥ/ጭ፤**

1. ቋንቋን በመልመድ ሂደት ቀዳሚው የቋንቋ ክሂል፣

ሀ. ንግግር ለ. ማዳመጥ ሐ. መፃፍ መ. ንባብ

2. ለመደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም ትኩረት የማይሰጥ የንግግር ክፍል፣

ሀ. ውይይት ለ. ጭውውት ሐ. ክርክር መ. እሰጣ ገባ

3. ብዙውን ጊዜ የምርምርና የጥናት ውጤቶችን ለማንበብ የምንጠቀምበት የንባብ ስልት፣

ሀ. የገረፍታ ንባብ ለ. የዝግታ ንባብ ሐ. የፍጥነት ንባብ መ. የአሰሳ ንባብ

4. ቅድመና ድህረ ግንድ ቅጥያ የተጨመረበት ቃል ፣

ሀ. የእሱ ለ. ስለሰበርኩ ሐ. ቤቴ መ. ከአዲስ አበባ

5. መስራች ቅጥያ የተጨመረበት ቃል፣ ሀ. ልብሴ ለ. ነገረኛ ሐ. እፅዋት መ. መምህራን

6. ከሚከተሉት ውስጥ ቅጥያ የማስጨምረው የቃል ክፍል፣
ሀ. ስም ለ. ቅፅል ሐ.ግስ መ. ተ/ግስ

7. ጠንከር ካለ ትዕዛዛዊ አ/ነገር መጨረሻ ላይ የሚገባው ስርዓተ ነጥብ፣

ሀ. አራት ነጥብ ለ. የጥያቄ ምልክት ሐ. ትዕምርተ አንክሮ መ. ትዕምርተ ስላቅ

8. ጥገኛ ሀረጎችን በውስጡ የሚይዝ የአ/ነገር ዓይነት፣ ሀ. ነጠላ አ/ነገር ለ. ተራ አ/ነገር
ሐ. ውስብስብ አ/ነገር መ. ድርብ አ/ነገር

9. በአንቀፅ ውስጥ በሀይለ-ቃሉ የተገለፀውን ዋና ሀሳብ የሚያብራሩ፣የሚያበለፅጉ አ/ነገሮች ፣

ሀ. መሪ አ/ነገር ለ. ሀይለ-ቃል ሐ. ደጋፊ አ/ነገር መ. ርዕሳዊ አ/ነገር

10. "ሁሉም መሳቂያ ነው ጊዜውን ሲስት፣

ብትርቀን አንወድም ለሚመለከት::" የሚለው ቅኔያዊ ግጥም ከየትኛው የቅኔ አይነት ይመደባል?

ሀ. ሰምና ወርቅ ቅኔ ለ. ህብር ቅኔ ሐ. ምርምር ቅኔ መ. የዋሸራ ቅኔ

11. "ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው::" ከሚለው ጋር በፍች የሚስማማው ምሳሌያዊ ንግግር፣

ሀ. ራስ ሳይጠና ጉተና ለ. አድሮ ቃሪያ ሐ. በደንባራ በቅሎ ቃጭል ተጨምሮ መ. የራስዋ ሲያርባት የሰው ታማስላለች

12. አማራጭን ለማቅረብ የሚያስችለው አያያዥ ቃል ፣ ሀ. አለበለዚያ ለ. በአጭሩ ሐ. ቢሆንም መ. ከዚህ ባሻገር

13. "ልጓም አጥባቂ" የሚለው ፈሊጣዊ ቃል ፍች፣ ሀ. ነገር የማይችል ለ. ህግ አክባሪ ሐ. ነገረኛ መ. ነጋዴ

14. ለበግ እዳሪ ቁጣጥ ካልን ፣ ለፍየል እዳሪ ________________ እንላለን:: ሀ. እበት ለ. በጠጥ ሐ. ሰፈፍ መ. ፋንድያ

15. ከታሪኩ መነሻ እስከ ፍፃሜው የሚዘልቅ የልቦለድ ገፀ ባህርይ፣

ሀ. አስተኔ ገፀባህርይ ለ. ፈርጀ ብዙ ገፀባህርይ ሐ. ፈርጀ አንድ ገፀባህርይ መ. ንዑስ ገፀባህርይ

16. የህሊና ግጭት እየተባለ የሚጠራው የልቦለድ ግጭት አይነት ፣

ሀ. ሰው ከማህበረሰቡ ለ. ሰው ከራሱ ሐ. ሰው ከተፈጥሮ መ. ሰው ከሰው

17. የግጭት ባህርይ የሆነው፣ ሀ. ፍልሚያ ለ. ተመጣጣኝነት ሐ. ዓላማ መ. ሁሉም

18. በመነገር ወይም በመተረት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈው ስነ-ቃል፣

ሀ. የሙሾ ቃላዊ ግጥም ለ. ፉከራና ቀረርቶ ሐ. አፈ-ታሪክ መ. የሰርግ ቃላዊ ግጥም

19. ለወተት ስልባቦት ካልን፣ ለወጥ ___________ እንላለን:: ሀ. ገፈት ለ. እፍታ ሐ. ሰፈፍ መ. መ/የለም

20. ቀድሞ የተፈፀመን ታሪክ አሁን ላይ በማምጣት/በማስገባት የሚቀርብ የልቦለድ አተራረክ ዘዴ፣

ሀ. ንግር ለ. ምልሰት ሐ. ገለፃ መ. ምልሰት

21. በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ያሉ አናባቢዎች ብዛት፣ ሀ. 5 ለ. 6 ሐ. 7 መ. 34

22. ወገን አመልካች ምዕላድ የተጨመረበት ቃል፣ ሀ. አንዲት ለ. መፅሀፍ ሐ. ኢትዮጵያዊ መ. ድንጋያማ

23. "ቤቶቹ" በሚለው ቃል ውስጥ ያሉት ቅጥያዎች የትኞቹ ናቸው? ሀ. ኣ - እና - ኤ ለ. -ኦቼ ሐ. -ኦቹ መ. ኦች-እና -ኡ

24. "ፈለጉ" በሚለው ቃል የሚገኘው ቅጥያ ትርጉም፣

ሀ. ብዙ ቁጥር አመልካች ለ. መደብ አመልካች ሐ. ባለንብረትነት አመልካች መ. ፆታ አመልካች

25. ከሚከተሉት መካከል ተራ አ/ነገር የሆነው፣

ሀ. ረዥም ሰው መጣ:: ለ. ሃይሉ የገዛው በግ ታረደ:: ሐ. ከበደ በሩጫ መጣ:: መ. "ሀ" እና "ሐ"

26. ከሚከተሉት ምርጫዎች መስተዋድድ የሆነው ቃል፣ ሀ. ነው ለ. እሱ ሐ. ሆነ መ. ስለ

27. "ሀይሉ በፍጥነት ኳሷን መታ::" በሚለው ዓ/ነገር ግሳው ሀረጉ፣

ሀ. በፍጥነት ለ. መታ ሐ. በፍጥነት ኳሷን መታ:: መ. ሀይሉ በፍጥነት

28. "ወረግቡ" የሚለው ፈሊጣዊ ቃል ፍች፣

ሀ. የወር ደሞዝ ለ. ልትወልድ የደረሰች ሴት ሐ. ቆንጆ መ. የወሩ መጨረሻ

29. "ጎባጣ ነህ አሉኝ ጎባጣ ነኝ ወይ፣

ከሰው አልጣላም ጀርባዬን ሳላይ::" በሚለው ቅኔያው ግጥም ውስጥ ህብረ ቃሉ፣

ሀ. ጎባጣ ነህ ለ. ከሰው አልጣላም ሐ. ጀርባዬን ሳላይ መ. አልጣላም

30. "ስጋ ቁጠር ቢሉት_______________::" ምሳሌያዊ ንግግሩን የሚያሟላው፣

ሀ. እሽ አለ ለ. ጣፍያ አንድ አለ ሐ. መቁጠር ተቸገረ መ. መብላት ጀመረ

31. ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ውስጥ የተለየ ትርጉም ያለው የትኛው ነው?

ሀ. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ ለ. አህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም ሐ. ትንሽ ስጋ እንደ መርፌ ትወጋ መ. የዘመድ ጥል የስጋ ትል

32. የልቦለድ ድርጊት የሚፈፀምበት ጊዜና ቦታ፣ ሀ. መቼት ለ. ግጭት ሐ. አንፃር መ. ሴራ

33. "አትኩራ ገብስ _____________________::" ምሳሌያዊ ንግግሩን የሚያሟላው፣

ሀ. ህዳር ሳይደርስ ለ. ጌሾ ሳይቀነጠስ ሐ. ጠላ ሳይጠነሰስ መ. ጎመን ባወጣው ነፍስ

34. "ክንዴን ሳልተራስ ማንም የሚደፍርህ የለም::" የተሰመረበት ቃል ፍች፣

ሀ. ሳልሞት ለ. ሳላንቀላፋ ሐ. የአልጋ ቁራኛ ሳልሆን መ. በደዌ ዳኛ ሳልያዝ

35. ከሚከተሉት ውስጥ አንድ ብቻ ፍች ያለው ቃል የትኛው ነው? ሀ. ነገረ ለ. አዛባ ሐ. ሰለሰ መ. መተረ

36. "እሽ አትበሉኝ የሹም ዶሮ ነኝ::" የሚለው ምሳሌያው ንግግር የሚገልፀው ፤

ሀ. አመለ ቢስነትን ለ. አትንኩኝ ባይነትን ሐ. ራስ ወዳድነትን መ. ገለልተኝነትን

37. የመጀመሪያው የአማርኛ ረጅም ልቦለድ ስራ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የጉሌለው ሰካራም ለ. ጦቢያ ሐ. አርዓያ መ. ፍቅር እስከ መቃብር

38. የነገሮችን ውስጣዊና ውጫዊ ባህሪ የሚገልፀው የቃል ክፍል፣ ሀ. ስም ለ. ግስ ሐ. ቅፅል መ. ተ/ግስ

39. "መረጠ" ከሚለው ግስ የተመሰረተው ውልድ ውጤታዊ ስም፣ ሀ. ምርጫ ለ. መምረጥ ሐ. ምርጥ መ. መምረጫ

40. ከስምና ከግስ በጥምረት የተመሰረተው ቃል ፤ ሀ. ቤተ ክርስቲያን ለ. አንጀት አርስ ሐ. ግንድ እግር መ. አይነ ልም

41. ከሚከተሉት ውስጥ ተሳቢ የሚያስፈልገው ሳቢ ግስ የቱ ነው? ሀ. ዛፈ ለ. በላ ሐ. ሞተ መ. "ሀ" ና "ለ"

42. መኖርን የሚገልፀው የግስ አይነት፣ ሀ. ሆነ ለ. ነበር ሐ. ነው መ. ናት

43. ብዙ ቁጥር አመልካች ቅጥያ የተጨመረበት ቃል፣ ሀ. የዋሆች ለ. ጥራጥሬ ሐ. መፅሀፎች መ. ሁሉም

44. ልቦለዱ ስለምን እንደሚያወራ ስንጠየቅ የምንመልሰው የልቦለዱ አላባ ፤ ሀ. ትልም ለ. ታሪክ ሐ. አንፃር መ. ገለፃ

45. ምንም አይነት ተራኪ ጣልቃ ሳይገባ የገፀባህርያት ንግግርና እንቅስቃሴ እንዳለ ተቀርፆ የሚቀርብበት የትረካ አንፃር፣

ሀ. 1ኛ መደብ አንፃር ለ. ሁሉን አወቅ አንፃር ሐ. ውሱን አወቅ አንፃር መ. ተውኔታዊ አንፃር

46. ከሚከተሉት ውስጥ የስነቃል ተግባር የሆነው፣ ሀ. መግለፅ ለ. ማስተማር ሐ. መቆጣጠር መ. ሁሉም

47. ዓላማው የተቃራኒን ቡድን ማሸነፍ የሆነ የንግግር ዘርፍ፣ ሀ. ውይይት ለ. ጭውውት ሐ. ክርክር መ. ምልልስ

48. ሁሉም ዓ/ነገሮች በአንቀፁ ውስጥ የተገለፀውን አንድ ሀሳብ ብቻ ማንሳት ያለባቸው መሆኑን የሚያሳየው የአንቀፅ ባህርይ፣

ሀ. ግጥምጥምነት ለ. ትኩረት ሐ. አንድነት መ. አፅንኦት

49. ቋንቋ ለሰው ልጅ ብቻ ተለይቶ የተሰጠ ፀጋ መሆኑን የሚገልፀው የቋንቋ ባህርይ፣

ሀ. ዘፈቀዳዊነት ለ. ሰብዓዊነት ሐ. ትዕምርታዊነት መ. ረቂቅነት

50. የመ/ቤት ደብዳቤ በምንፅፍበት ጊዜ የግድ መካተት ያለበት፣

ሀ. ግልባጭ ለ. ፊርማ ሐ. አባሪ መ. ሁሉም

51. አንድ ሰው ለራሱ/ለግሉ ሲያነብ የሚጠቀምበት የንባብ አይነት፣

ሀ. የለሆሳስ ንባብ ለ. ድምፃዊ ንባብ ሐ. ድምፅ አልባ ንባብ መ. "ሀ" ና "ሐ"

52. ረጅምነትን ለመግለፅ የምንጠቀምበት ፈሊጣዊ አገላለፅ፣ ሀ. ብቅል አውራ ለ. የማሪያም ጉድ ሐ. ሰማይ ዳሱ መ. "ሀ"ና "ሐ"

53. በእጅ ፅህፈት ወቅት የተረሳን /የተዘለለን ሀሳብ ለማስገባት የሚያገለግለው ስርዓተ ነጥብ ፣

ሀ. ዕሩይ ለ. ረድፍ ሐ. እመጫት መ. ጭረት

54. ቀጥሎ ከተዘረዘሩት አማራጮች መካከል የረጅም ልቦለድ ባህርይ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ጠባብ መቼት ለ. ከአንድ በላይ ጭብጥ ሐ. በርካታ ገፀባህርያት መ. ሰፊ የገፀባህርያት ገለፃ

55. አንድን ጉዳይ ብቻ መርጦ በትኩረት የሚያይ መሆኑን የሚያሳየው የአጭር ልቦለድ ባህርይ፣

ሀ. ቁጥብነት ለ. ነጠላ ውጤት ሐ. ጥድፊያ መ. ውስብስብነት

56. "እጀ ሰባራ" የሚለው ፈሊጣዊ ቃል ፍች፣ ሀ. ጥሩ ነገር የማይሰራ ለ. በሽተኛ ሐ. ገንዘብ ቆጣቢ መ. ልፍስፍስ

57. የመጨረሻው ትርጉም ያለውና ወደ ሌላ ትርጉም ወዳለው አሀድ ሊከፈል የማይችል የቋንቋ ቅንጣት፣

ሀ. ቃል ለ. ምዕላድ ሐ. ቅጥያ መ. ሀረግ

58. በጭውውት ጊዜ የገፀባህርያት ምልልስ ተለይቶ የሚቀመጠው፣

ሀ. በድርብ ትዕምርተ ጥቅስ ለ. በነጠላ ትዕምርተ ጥቅስ ሐ. በቅንፍ መ. በነጠላ ሰረዝ

59. "ቆቅ" የሚለው ቃል ፍካሪያዊ ፍች፣ ሀ. ስጋዋ የሚበላ የወፍ ዝርያ ለ. ንቁ ሐ. ምላሳም መ. መሰሪ

60. “እስከ” የሚለውን ቃል ተክቶ የሚገባው ስርዓተ ነጥብ፣ ሀ. አብይ ሰረዝ ለ. ንዑስ ሰረዝ ሐ. እዝባር መ. ነቁጥ

61. “ህቡዕ” የሚለው ቃል ተቃራኒ ፍች፣ ሀ. ስውር ለ. ግልፅ ሐ. ሚስጥር መ. አስቸጋሪ

62. ስነምግባርን ለህፃናት ለማስተማር የሚያገለግለው ስነ ቃል፣ ሀ. ተረት ለ. ሀተታ ተፈጥሮ ሐ. እንቆቅልሽ መ. እንካስላንትያ

63. ውስብስብ የሆነው የቋንቋ ክሂል ፣ ሀ. ማድመጥ ለ. ፅህፈት ሐ. ንግግር መ. ንባብ

64. የሰው ልጅ ሊግባባት የሚችለው የመግባቢያ ዘዴ፣

ሀ. ቋንቋ ለ. ምልክት ሐ. እንቅስቃሴ መ. ሁሉም

65. የኢትዮጵያ መንግስት የስራ ቋንቋ ፣ ሀ. ኦሮምኛ ለ. አማርኛ ሐ. ትግርኛ መ. እንግሊዘኛ

66. ሲጠብቅና ሲላላ ሁለት ፍች የሚሰጠው ቃል፣ ሀ. ሰፊ ለ. ማቅ ሐ. ማረሻ መ. ሁሉም

67. ዋና ስምን ከተጣማር ስም ለመለየት የሚያገለግለው ስርዓተ ነጥብ ፣

ሀ. ድርብ ሰረዝ ለ. ነጠላ ሰረዝ ሐ. አንድ ነጥብ መ. ትዕምርተ ጥቅስ

68. “በቤቷ ቀጋ፣________________________________::” ምሳሌያዊ ንግግሩን የሚያሟላው ፣

ሀ. በውጭ መንጋጋ ለ. በውጭ ሰንጋ ሐ. በውጭ አልጋ መ. በርጥብ ፍለጋ

69. “አስቴር <u>ንብ</u> ናት::” የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍል ፣ ሀ. ግስ ለ. ስም ሐ. ቅፅል መ. ተ/ ግስ

70. “ቤታችን” በሚለው ቃል ውስጥ ያለው ቅጥያ ተግባር፣

ሀ. ንብረት አመልካች ለ. ቁጥር አመልካች ሐ. መደብ አመልካች መ. ፆታ አመልካች

71. “ተቆጣኝ” በሚለው ቃል ተሳቢ አመልካች ቅጥያው የቱ ነው? ሀ. —ጣ ለ. -ጣኝ ሐ. -ኝ መ. -ኣኝ

72. የወል ስም የሆነው ቃል የቱ ነው? ሀ. በግ ለ. ዳሽን ተራራ ሐ. ባሮ ወንዝ መ. አስቴር

73. “ሂያጅ” የሚለው ፈሊጣዊ ቃል ፍች፣ ሀ. አመንዝራ ለ. ወላዋይ ሐ. መንገደኛ መ. ሯጭ

74. ከሚከተሉት ውስጥ የክቡር ሀዲስ አለማዬሁ ስራ ያልሆነው የቱ ነው

ሀ. ፍቅር እስከ መቃብር ለ. ኦሮማይ ሐ. ወንጀለኛው ዳኛ መ. ትዝታ

75. ሰምና ወርቁን በአንድ ቃል አጣምሮ የሚይዝ የቅኔ አይነት፣

ሀ. ሰምና ወርቅ ቅኔ ለ. ህብር ቅኔ ሐ. ምርምር ቅኔ መ. መ/ የለም

76. አንባቢው የሚፈልገውን መፅሀፍ በባለሙያ ድጋፍ የሚያገኝበት የቤተ መፅሀፍት አጠቃቀም ዘዴ፣

ሀ. ዝግ ዘዴ ለ. ክፍት ዘዴ ሐ. ካታሎግ መ. "ለ" ና "ሐ"

77. "በደረሰብኝ ግፍና በደል ሆዴ ሻከረ::" የተሰመረበት ቃል ፍች፣ ሀ. ነገር ገባኝ ለ. ብርታቱን አገኘሁ ሐ. ቂም ያዝኩ መ. "ሀ ና"ሐ"

78. አንድ መዝገበ ቃል በውስጡ የሚይዘው፣ ሀ. የቃላት ፍች ለ. የቃላት ርባታ ሐ. ስርዓተ ነጥብ መ. ሁሉም

79. "ሁልግዜ ጧት ጧት ስፖርት እሰራለሁ::" የዚህ አ/ነገር ባለቤት፣

ሀ. ስፖርት ለ. እኔ ሐ. ሁልግዜ ጧት ጧት መ. ሁልግዜ ጧት ጧት ስፖርት

80. "ልጁ በሰራው ስራ ድል ተቀዳጀ::" የተሰመረበት ቃል ፍች፣ ሀ. መጎናፀፍ ለ. መሸነፍ ሐ. ኊላ መቅረት መ. ስሙ ተነሳ

81. "እኔ ከአይኔ በቀር በሽታ የለኝም፣

ሀኪሙም ቢያክመኝ ጋርዶ አለቀቀኝም::" የዚህ ቅኔያዊ ግጥም ህብረ ቃል፣

ሀ. ከአይኔ በቀር ለ. ጋርዶ ሐ. ሀኪሙም ቢያክመኝ መ. ጋርዶ አለቀቀኝም

82. ከምንጩ የተወሰደ ሀሳብ በራስ አገላለፅ ፣ስልትና ለዛ አጥሮ ሲቀርብ________________ ይባላል::

ሀ. ግለ ገለፃ ለ. ጭምቅ ሀሳብ ሐ. ቀጥተኛ ጥቅስ መ. ረጅም ጥቅስ

83. በድርብ ቃላት መካከል የሚገባው ስርዓተ ነጥብ ፣ ሀ. አብይ ሰረዝ ለ. ንዑስ ሰረዝ ሐ. ጭረት መ. እዝባር

84. ከአንድ በላይ ርዕሰ ጉዳይ በአንድ ጊዜ የሚስተናግድበት የንግግር ዘርፍ ፣ ሀ. ጭውውት ለ. ክርክር ሐ. ውይይት መ. እሰጣገባ

85. ሹፈትን፣ስላቅን፣ሳቅን፣ነቀፋን፣ወዘተ. የመሳሰሉ አቃቂረኛ ስሜቶችን ለማመልከት የሚገባው ስርዓተ ነጥብ ፣

ሀ. ትዕምርተ አንክሮ ለ. ትዕምርተ ስላቅ ሐ. ዕሩይ መ. ጭረት

86. ነገሮችን በደረጃ ለማስቀመጥ የሚያገለግለው አያያዥ ቃል፣ ሀ. በተቃራኒው ለ. ቢሆንም ሐ. በመጀመሪያ መ. በተለይ

87. የአንድን ነገር ባህሪ ፣ድርጊትና ችሎታ በቀጥታ ለሌላ አካል በመስጠት የሚፈጠር ዘይቤ ፣

ሀ. አነፃፃሪ ዘይቤ ለ. ለዋጭ ዘይቤ ሐ. ሰወኛ ዘይቤ መ. ተምሳሌት ዘይቤ

88. ከሚከተሉት ውስጥ ተ/ግሳዊ ሀረግ የሆነው፣ ሀ. በጣም ክፉኛ ለ. እንደገና መጣ ሐ. የስንዴ ዳቦ መ. እንደወንድሙ ጥቁር

89. ከሚከተሉት ውስጥ በቅርፁ /-ኦች/ የሚለውን አብዥ ምዕላድ የማይቀበለው፣ ሀ. ስም ለ. ግስ ሐ. ቅፅል መ. መ/ የለም

90. የስነቃል ባህርይ ያልሆነው፣ ሀ. ክዋኔ ለ. ቃላዊነት ሐ.ፅሁፋዊነት መ.ቡድናዊነት

91. ነጥሎ የማንበብ ልምድ የሚዳብርበት የንባብ ስልት፣ ሀ. የአሰሳ ንባብ ለ. የፍጥነት ንባብ ሐ. የዝግታ ንባብ መ. ሰፊ ንባብ

92. አዝናኝለት ያለው፣ግዜና ቦታ የማይወስንለት የንግግር ዘርፍ፣ ሀ. ውይይት ለ. ክርክር ሐ. ጭውውት መ. እሰጣገባ

93. ከሚከተሉት መካከል የስነ ቃል ባህርይ ያልሆነው፣ ሀ. ቡድናዊነት ለ. ፅሁፋዊነት ሐ. ተለዋጭነት መ. ተከዋኝነት

94." ብዙ <u>ዲያቆናት</u> በሰርጉ ላይ አልተገኙም::" ከተሰመረበት ቃል ጋር በቅርፅ የማይመሳሰለው ፣

ሀ. አመታት ለ. ካህናት ሐ. ወራት መ. ሊቃውንት

95. "ወፍ" የሚለው ቃል የግዕዝ ብዜት የቱ ነው? ሀ. አዕዋፍ ለ. ወፎች ሐ. አዕዋፍት መ. አዕዋፍቶች

96. "<u>የተሸለመው</u> ልጅ ንግግር አደረገ::" የተሰመረበት ቃል ተግባር ፣

ሀ. የግስ ገላጭ ለ. የስም ገላጭ ሐ. የቅፅል ገላጭ መ. የገላጭ ገላጭ

97. በልቦለድ ገፀባህርያት መካከል የሚደረገው ግጭት መቋጫ ምን ይባላል? ሀ. ልቀት ለ. ንረት ሐ. ጡዘት መ. መደምደሚያ

98. ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ፍንጭ የሚሰጥበት የልቦለድ ዘዴ ፣ ሀ. ምልልስ ለ. ንግር ሐ. ምልሰት መ. ገለፃ

99. በአ/ነገር ውስጥ ማሰሪያ አንቀፅ በመሆን የሚያገለግለው የቃል ክፍል ፣
ሀ. ግስ ለ. ስም ሐ. ቅፅል መ. ተ/ግስ

100.“ ______________________በህልሙ አቁማዳ ይዋስ።” ባዶ ቦታው ላይ የሚገባው ፣

ሀ. ለማኝ ለ. ድሃ ሐ. መለመን የለመደ ምላስ መ. ችግረኛ

# “ራሳችንን ከኮረና ቫይረስ እንጠብቅ፤ ትምህርታችንን በቤታችን ሆነን እንከታተል!!!”